# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

| | |
|---|---|
| ተዛማጅ ምንጮች፡- | ABC-RA, BLB, JEA, JEA-RA, JEA-RB, JEA-RC, JEA-RE, JFA-RA, JOA-RA, KLA-RA |
| ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፡- | የትምህርት ቤቶች ድጋፍ እና ማሻሻል ቢሮ/Office of School Support and Improvement |

## የቤት አልባ ተማሪዎች የት/ቤት ምዝገባ

I. **አላማ**

የመኖሪያ ቤት እጦት ያጋጠማቸው ልጆች እና ወጣቶች ለሌሎች ሕፃናት እና ወጣቶች እንደሚሰጣቸው ቅድመ ት/ቤትን ጭምር እኩል ነፃ እና ተገቢ ህዝባዊ ትምህርት እንዲያገኙ የፌዴራል እና የስቴት መስፈርቶችን ተግባራዊ ለማድረግ

በፌደራል ህግ በተደነገገው መሠረት ቤትአልባ ህጻናት እና ወጣቶች ትምህርት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት ስላለባቸው ሁሉም የስቴት ተማሪዎች የሚያልፉበትን ጠንካራ የትምህርት ስኬት ደረጃዎችን እንዲያሟሉ የሚጠበቀው ሁኔታ ተደራሽ መሆኑን ለማረጋገጥ

ቋሚ፣ መደበኛ እና በቂ የምሽት ማደሪያ ለሌላቸው እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለመከታተል ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የተረጋጋ የትምህርት አካባቢን በመስጠት ት/ቤት እንዲገቡ ለማድረግና ለማቆየት እና በተቻለ መጠን የመንቀሳቀስ ሁኔታቸው በአካዳሚክ ስኬታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ለመቀነስ

ቤት አልባ ህጻናት እና ወጣቶችን በመለየት ትምህርት ቤት ተመዝግበው እንዲማሩና በትምህርታቸው ላይ ለማቆየት እና ትምህርታቸውን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ለማድረግ፥ ህጻናትን እና ወጣቶችን በክፍያ፣ በቅጣት፣ ወይም ከት/ቤት መቅረት ምክንያት ትምህርት እንዳይቀጥሉ የሚከለክሏቸውን እንቅፋቶች ለማስወገድ እና በትምህርታቸው ላይ እንዲቆዩ ለማስቻል

II. **ጉዳዩ**

የቤት እጦት ላጋጠማቸው ተማሪዎች የፌደራል ሕጎች የሚከተሉትን መብቶች ይደነግጋሉ።

A. በ 1987 የወጣው የፌደራል ማኪኒ-ቬንቶ ቤት አልባ የእርዳታ ህግ/McKinney-Vento Homeless Assistance Act (የማኪኒ-ቬንቶ ህግ ወይም MKV) የቤት እጦት ለሚያጋጥማቸው ህጻናት እና ወጣቶች የሚከተሉትን መብቶች እና አገልግሎቶች ይሰጣል፡-

1. ተፈላጊ ሠነዶች ወይም ኃላፊነት ሚወስድላቸው ሰው ባይኖሯቸውም ህጻናት እና ወጣቶች በፍጥነት ትምህርት ቤት ለመመዝገብ፣(ከዚህ በታች እንደተገለፀው) አሳዳጊ/ተንከባካቢ እንዳላቸው ማረጋገጫ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም።

2. በነበሩበት የቀድሞ ት/ቤታቸው የመቆየት መብት (ከዚህ በታች እንደተገለጸው ተማሪው(ዋ) ቀደም ሲል በተመዘገበ(ች)በት ትምህርት ቤት)።

3. ከቀድሞ ትምህርት ቤታቸው ያለው የመጓጓዣ ርቀት ሁኔታ። ከትምህርት ሰዓት በኋላ ለሚካሄዱ ፕሮግራሞች ወይም ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ለሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ለተማሪዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ፣ ለ MKV ብቁ የሆኑ ተማሪዎችም የመጓጓዣ አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው።

4. በነጻ እና የቅናሽ ዋጋ የምግብ ፕሮግራም ውስጥ በቀጥታ መመዝገብ።

5. ታይትል I አገልግሎቶችን፣ የምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎቶችን፣ ወይም ተመሳሳይ የስቴት ወይም የአካባቢ አገልግሎቶችን ጨምሮ በት/ቤት ለሚገኙ ተማሪዎች ከሚሰጡት አገልግሎቶች ጋር ተመጣጣኝ አገልግሎቶችን ማግኘት፣

6. የማግኔት ፕሮግራሞችን፣ የሠመር ትምህርትን፣ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርትን፣ የበለፀገ እና የተፋጠነ ትምህርትን፣ በኦንላይን መማር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ በሁሉም የት/ቤት ፕሮግራሞች እና ተግባራት ውስጥ ተደራሽነት እና ሙሉ ተሳትፎ ይኖራቸዋል።

7. ስለ አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ትምህርት ህግ (IDEA) የእንግሊዘኛ ቋንቋ ማዳበር ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አላቸው።

B. የሚረዳቸው ሰው ለሌላቸው ወጣቶች የድጋፍ አገልግሎት

1. MKV ብዙውን ጊዜ ትምህርት ቤት ለመግባት/ለመማር፣ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎቶች የማያገኙ፣ እና በት/ቤት ስኬታማ ለመሆን የተለያዩ መሰናክሎች የሚያጋጥሟቸው ቤት አልባ የሆኑ ኃላፊነት የሚወስድላቸው ሰው የሌላቸው ወጣቶችን ተጋላጭነት ለመቀነስ ይፈልጋል። ስለ እነርሱ የሚከራከር እና የወላጅ መብቶችን መጠቀም የሚችል ወላጅ/አሳዳጊ ከሌላቸው፣ የት/ቤት ምዝገባ ሊከለከሉ፣ ረዘም ላለ ጊዜ ከትምህርት ገበታቸው ታግደው ሊቆዩ፣ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተገቢው ጊዜ ላይመረቁ ወይም ከቶም የመመረቅ እድል ላይኖራቸው ይችላል።

2. IDEA ክፍል B ላይ በተገለፀው መሠረት፣ የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች፣ ትምህርት ቤቶች ጭምር ወላጅ/አሳዳጊ ለሌለው (ለሌላት) ቤት አልባ ወጣት የወላጅ ምትክ ወይም ተተኪ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የወላጅ ምትክ እስኪሾም ድረስ፣ በአግባቡ የድንገተኛ ጊዜ መጠለያ ሰራተኞች፣ የሽግግር ወቅት መጠለያ፣ ተናጠል የመኖሪያ ፕሮግራሞች፣ ጎዳና ተዳዳሪዎችን የሚረዱ ፕሮግራሞች ሁሉ IDEA መስፈርቶች አሟልተው በጊዜያዊነት የወላጅ/የአሳዳጊ ተተኪ ሆነው ሊሰየሙ ይችላሉ።

C. የክርክር አፈታት፡ የማኪኒ-ቬንቶ ህግ/McKinney-Vento Act ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ጠባቂ የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች ብቁነትን፣ የት/ቤት ምዝገባን፣ ወይም የትምህርት ቤት ምርጫን በሚመለከት በተወሰደ እርምጃ ላይ መከራከር እና ለክርክሩ መፍትሄ እስኪገኝ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ተማሪው(ዋ) እንዲቆይ/እንድትቆይ በሚፈልጉበት ቦታ እንዲቀጥል/እንድትቀጥል የመጠየቅ መብት ይሰጣቸዋል።

D. ብቁነትን ማረጋገጥ፡ የተማሪን MKV ብቁነት በመወሰን ሂደት ላይ፣ የት/ቤት ዲስትሪክቶች ስለ ልጁ/ልጅቱ ወይም ስለ ወጣቱ(ቷ) የኑሮ ሁኔታ መረጃን ለማረጋገጥ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ነው ብለው የሚያምኑባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላል። እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሲኖሩ ዲስትሪክቶች ጥረቶች ሁሉ ምክንያታዊ መሆናቸውን በጥንቃቄ እና የሌሎችን ስሜት በመረዳት ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን እና የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ህጉን የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

## III. ትርጉም

A. ዋነኛ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ውሳኔ (BID) ማለት፡- ቤት አልባ ተማሪ የሚማርበትን/የምትማርበትን ትምህርት ቤት የመምረጥ ሂደትን ይመለከታል። ተማሪው/ዋ በነበረ(ች)በት የቀድሞ ት/ቤቱ(ቷ) እንዲቆይ/እንድትቆይ ማድረግ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ በሌለው/በሌላት ቤት አልባ ወጣት የቀረበ

ጥያቄን የሚቃረን ካልሆነ በስተቀር፣ ትምህርት ቤቶች ለ MKV ብቁ የሆነ/ች ተማሪን በነበረ(ች)በት የቀድሞ ት/ቤቱ(ቷ) እንዲቆይ/እንድትቆይ ማድረግ ለተማሪው(ዋ) ይበልጥ ይጠቅማል ተብሎ የሚታመንበትን ማድረግ መሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚኖርባቸው ይደነግጋል። ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ መመዝገብ በሚፈልጉበት ት/ቤት እና MCPS ለተማሪው(ዋ) ይጠቅማል ብሎ በሚያምንበት ትምህርት ቤት መካከል ልዩነት ሲፈጠር BID ስብሰባ ይጠራል። ሰክሽን IV.C. ይመልከቱ።

1. በመኖርያ አካባቢ የሚገኝ ትምህርት ቤት ማለት

    a) ተማሪው(ዋ) በቋሚነት በኖረ(ች)በት ጊዜ የተማረ(ች)በት ትምህርት ቤት፣ ወይም

    b) ተማሪው(ዋ) ለመጨረሻ ጊዜ የተመዘገበ(ች)በት ትምህርት ቤት ነው።

2. አንድ ተማሪ ቀድሞ በተማረ(ች)በት ትምህርት ቤት የሚሰጠውን የመጨረሻውን የክፍል ደረጃ ካጠናቀቀ(ች) ትምህርት ቤቱ የተመደበበትን መጋቢ ትምህርት ቤት ያካትታል።

3. የአካባቢ ትምህርት ቤት ማለት፡- በተማሪው(ዋ) ጊዜያዊ የመኖሪያ ቤት አድራሻ የሚገኝን አካባቢ የሚያገለግል ትምህርት ቤት ነው።

B. ልጅ/ወጣትማለት በሜሪላንድ ውስጥ የሕዝብ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት መርሃ ግብር ለመከታተል ብቁ የሆነ(ች) ግለሰብ ማለት ነው — (የሚከተሉትን ጨምሮ)

1. ከቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል፣

2. ሄድስታርት ወይም ኢቨን ስታርት

3. ልዩ ትምህርት፣እክል ያለባቸው ህጻናት እና ታዳጊዎች የቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም (Child Find) ጨምሮ፣ ወይም

4. ሌሎች ፕሮግራሞች

C. McKinney-Vento Act (MKV) ብቁ ተማሪ ማለት- ቋሚ፣መደበኛ እና በቂ መኖሪያ የሌለው/የሌላት ልጅ ወይም ወጣት፣ የቅድመ ትምህርት ቤት እድሜ ያለው/ያላትን ልጅ ጨምሮ ጊዜያዊ መኖሪያ ቤቱ(ቷ) የሚገኘው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ቢሆንም/ባይሆንም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለመሳተፍ ብቁ የሆነ(ች) ማለት ነው። ይህ ቃል የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

1. ህጻናት ልጆች እና ወጣቶች—

    a) በመኖሪያ ቤት እጦት፣ በኢኮኖሚ ችግር ወይም በተመሳሳይ ምክንያት የሌሎች ሰዎችን መኖሪያ ቤት መጋራት፤

    b) ሌላ አማራጭ ወይም በቂ ማረፊያ ስለሌላቸው በሞቴል፣ በሆቴል፣ በተጎታች ፓርክ ወይም በካምፕ መሬት ውስጥ መኖር፤

    c) በአስቸኳይ ሁኔታ ወይም በጊዜያዊ መጠለያ ውስጥ መኖር[1]፣ ወይም

---

[1]የማደጎ እንክብካቤ ምደባን የሚጠብቅ-የምትጠብቅ ልጅ ወይም ወጣት እንደ ቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት አይቆጠርም። በማደጎ ያሉ ተማሪዎችን በተመለከተ ለበለጠ መረጃ የቦርድ ፖሊሲ JEA መኖሪያ፣ የትምህርት ክፍያ እና ምዝገባ፣ MCPS ደንብ JEA-RB የተማሪዎች ምዝገባ፣ ደንብ JEA-RE የትምህርት ክፍያ ላይ የተመሰረተ ምዝገባ፣ እና ደንብ JOA-RA የተማሪ ሪኮርዶችንምይመልከቱ።

d) በሆስፒታል ውስጥ የተጣለ(ች)።

2. መሠረታዊ የሌሊት መጠለያ ያላቸው ልጆች እና ወጣቶች—

a) መኪና፣ መናፈሻ፣ የሕዝብ መዝናኛ ቦታ፣ ወና የተተወ ሕንፃ፣ አውቶቡስ ወይም ባቡር ጣቢያ፣ ወይም ተመሳሳይ መቼት ለሰው ልጆች እንደ መደበኛ መጠለያ ሆኖ ያልተዘጋጀ ወይም በተለመደው አይነት ለመኖሪያነት ጥቅም ላይ ያልዋለ የሕዝብ ወይም የግል ቦታ፤ ወይም

b) ውሃ፣ ኤሌክትሪክ፣ ወይም ሙቀት የመሣሰሉ ቤተሰብ፣ ልጅ፣ ወይም ወጣት የሚኖሩበት ሁኔታ መሠረታዊ መገልገያ አለመኖሩን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን የሚችል ዝቅተኛ ደረጃ ያለው መኖሪያ እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠር፤ በተባይ ወይም ሻጋታ የተበከለ እና የሥራ ማእድ ቤት ወይም መጸዳጃ ቤት የመሳሰለ መሠረታዊ መገልገያ የሌለው፤ ወይም ለአዋቂዎች፣ ለልጆች ወይም ለአካል ጉዳተኞች አደጋ ሊያስከትል-ሊደቅን የሚችል ስፍራ።

3. ፈልሰው የመጡ የግብርና ሠራተኞች ወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች በአንዱ የሚኖሩ ልጆች፤ ወይም

4. አንድጠባቂ የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣትማለት፡- በወላጅ/አሳዳጊ አካላዊ ጥበቃ ውስጥ ያልሆነ(ች) ተማሪ ማለት ነው።

D. MKV አገናኝ/liaison ማለት MKV-ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ተለይተው፣ ት/ቤት ተመዝግበው ተገቢ የሆኑ የትምህርት አገልግሎቶችን ሁሉ ማግኘታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበ(ባ)ት ሰው ነው/ናት። MKV አገናኝ/liaison MKV አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አቀንቃኞች እና የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ስለ አገናኝነት ተግባራት የማሳወቅ እና በዋና አገናኝነት የማገልገል ሃላፊነት እንዳለበት ማሳወቅ አለበ(ባ)ት። የግንኙነት ኃላፊው(ዋ)ን/liaison በአለምአቀፍ የተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ ክፍል (IAE) በስልክ ቁጥር 240-740-4511 ማግኘት ይቻላል።

E. ወላጅ/አሳዳጊ ማለት –

1. MKV አገልግሎት ለማግኘት ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ህጋዊ ወይም አካላዊ ጥበቃ የማድረግ ኃላፊነት ያለው/ያላት ወላጅ፣ ግለሰብ ወይም የማህበረሰብ ኤጀንሲ፣

2. በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሕፃን ወይም የወጣት ሞግዚትነት የተሰየመ(ች) ሰው ወይም የማህበረሰብ ኤጀንሲ፣ ወይም

3. የወላጅ መብቶችን የሚጠቀም ተንከባካቢ የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ተማሪ።

## IV. የአሠራር ቅደምተከተል

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች፣ MCPS ደንቦች እና ተዛማጅ አፈጻፀሞች፣ቋሚ፣ መደበኛ፣ እና ተገቢ የምሽት ማደሪያ የሌላቸው እና በ MCPS ለመማር ብቁ የሆኑ ህጻናትን እና ወጣቶችን ለመመዝገብ፣ለመማር፣ ወይም ለትምህርታዊ ስኬት እንቅፋት ሆነው መስራት የለባቸውም።

A. ወዲያውኑ የሚደረግ ምዝገባ

1. ለ McKinney-Vento ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ወዲያውኑ መመዝገብ እና በወላጅ/አሳዳጊ ወይም ጠባቂ የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት እንዲማር ወደሚፈለግበት ትምህርት ቤት እንደአግባቡ የመጓጓዣ አገልግሎት መስጠት አለበት።

2. ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ/ጠባቂ የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች፣ MCPS ቅጽ 560-24፣ አዲስ የተማሪ መረጃ ሲሞሉ የጋራ መኖሪያ ቤት ሳጥን ላይ ምልክት ካደረጉ፣ ተማሪው(ዋ) ቋሚ፣ መደበኛ፣ እና ተገቢ የሆነ የምሽት መኖሪያ እንደሌለው/እንደሌላት ለማረጋገጥ ትምህርት ቤቱ/ተወካዩ የበለጠ መጠየቅና ማጣራት ያስፈልጋል።

3. ምንም እንኳን ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች በመደበኛነት ለምዝገባ የሚያስፈልጉትን የትምህርት ማስረጃዎች፣ የልደት ምስክር ወረቀት፣ የክትባት ማስረጃ እና የአሳዳጊነት ሠነዶችን ማቅረብ ባይችሉም፣ትምህርት ቤቱ ወዲያውኑ ተማሪው(ዋ)ን መቀበል/መመዝገብ እና ተማሪው(ዋ) በመጨረሻ ከተማረ(ች)በት ትምህርት ቤት አስፈላጊ የትምህርት እና ሌሎች መረጃዎችን ማግኘት አለበት። ትምህርት ቤቱ ተማሪው(ዋ)ን ከመመዝገቡ በፊት እነዚያ ማስረጃዎች እስኪቀርቡ ድረስ መጠበቅ የለበትም።

4. በትምህርት ቤት ምዝገባ ላይ አለመግባባት ከተፈጠረ፡-

   a) ተንከባካቢ የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት ከሆነ(ች)፣አለመግባባቱ እስኪፈታ ድረስ MKV ግንኙነት ኃላፊው(ዋ)/ተወካይ ተማሪው(ዋ) ወዲያውኑ ት/ቤት ተመዝግቦ(ባ) ወደፈለገ(ች)ው ትምህርት ቤት የመጓጓዣ አገልግሎት መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት።

   b) ክርክሩ መፍትሔ እስከሚያገኝ ድረስ፣ ማንኛቸውንም የይግባኝ ሂደቶችን ጨምሮ፣ በክርክር አፈታት ሂደቱ ወቅት፣ ተማሪው(ዋ) መመዝገብ በፈለገ(ች)በት ትምህርት ቤት ትምህርት ይቀጥላል፤ እና MCPS የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

5. ለ MKV-ብቁ የሆነው/የሆነችው ተማሪ የክትባት ወይም የህክምና ማስረጃዎችን ማግኘት ከፈለገ/ች፣ መዝጋቢው ትምህርት ቤት ወዲያውኑ ወላጁ/አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ የሌለውን/የሌላትን ቤት አልባ ወጣት ወደ MKV ግንኙነት ኃላፊ ይልካል፣ እርሱ(ሷ)ም አስፈላጊውን የክትባት ወይም የህክምና ማስረጃዎችን እንዲያገኝ/እንድታገኝ ማመቻቸት አለበ(ባ)ት።

B. በMcKinney-Vento Act ላይ ስለተቀመጡት መብቶች ብቁ ስለመሆን

1. በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚማሩ ተማሪዎች

   የ MCPS ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ቤተሰብ ቋሚ፣ መደበኛ እና ተገቢ የሆነ የምሽት ማደሪያ እንደሌለው ከገለጸ ወይም በመኖሪያ ቤት አልባነት ምክንያት ተማሪው(ዋ)ን ከትምህርት ቤት ለማስወጣት የሚሞክሩ ከሆነ፣ ወደፊት እስከሚረጋገጥ ድረስ ተማሪው(ዋ) MKV-ብቁ ነው/ናት ተብሎ ሊታሰብ ይገባል።

2. ጠባቂ የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች

   a) ሬጅስትራሮች እና ሌሎች የምዝገባ ሰራተኞች በወላጆች/አሳዳጊዎች አካላዊ ጥበቃ ስር ያልሆኑ ተማሪዎችን ለመለየት የመመዝገቢያ ቅጾችን ይገመግማሉ፤ እና ተማሪው(ዋ)

ለት/ቤት ምዝገባ፣ የመማር መብቶቻቸውን ለመረዳት፣ እና ማግኘት የሚችሏቸውን ድጋፎችን እና አገልግሎቶችን ለማግኘት ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል ለሚመለከተው አማካሪ እና MKV ግንኙነት ኃላፊ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለባቸው።

b) MKV ግንኙነት ኃላፊ/ተወካይ ረዳት የሌላቸውን ቤት አልባ ወጣቶችን በሚመለከት፣ ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን ለመወሰን በሚደረጉ ስብሰባዎች፣ ክሬዲቶችን በማስተላለፍ፣ እና ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን በማግኘት ረገድ መርዳት አለበ(ባ)ት። የ MKV አገናኝ ኃላፊነቶችን ዝርዝር ለማየት ሰክሽን IV.G ይመልከቱ።

c) አማካሪዎች ረዳት ለሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምረቃ፣ ለኮሌጅ እና ለስራ እንዲዘጋጁ እና እንዲያሻሽሉ ምክር መስጠት አለባቸው።

d) MKV አገናኝ/ወኪል፣ የትምህርት ቤት ካውንስለሮች፣ የተማሪ ሰራተኞች (PPWs)፣ እና ከኮሌጅ ዝግጁነት ጋር የተያያዘ ሀላፊነት የተሰጣቸው ሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ለሁሉም ቤት አልባ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የኮሌጅ እና የስራ ዝግጁነትን፣ የኮሌጅ ምርጫን፣ የማመልከት ሂደቱን (የፌዴራል የተማሪ ፋይናንሻል እርዳታ ማመልከቻን ጨምሮ) እና በካምፓስ ውስጥ የሚገኙ ድጋፎችን በተመለከተ መረጃ እና ግላዊ ምክር ለመስጠት ተባብረው መስራት አለባቸው። እንዲሁም ተማሪዎች ትራንስክሪፕት እና ዲፕሎማ እንዲያገኙ መርዳት እና የከፍተኛ ትምህርት ህግ ድንጋጌን ጨምሮ የፌዴራል፣ የስቴት፣ እና ሌሎች ድጋፎችን ማግኘት እንዲችሉ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የሚማሩ ተማሪዎች ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የማግኘት መብታቸውን ማሳወቅ አለባቸው።

4. ከላይ ባሉት ሂደቶች መሰረት አንድ ተማሪ ቤት አልባ መሆኑ(ኗ) የሚገመት ቢሆንም፣ ይህ ግምት ትክክል አለመሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከመጣ McKinney-Vento Act ብቁ የመሆን መብቶች በ IAE ዳይሬክተር ውሳኔ ሊሻር ይችላል። በእነዚህ ሁኔታዎች፣ MCPS ሁሉም እንደዚህ ያሉ ጥረቶች ምክንያታዊ መሆናቸውን፣ በፍላጎት እና በጥንቃቄና በማስተዋል የመወሰን መብት ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን እና የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ህግ ድንጋጌን መሰረት ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት (FERPA)።

5. MKV ብቁነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ፣ተማሪው(ዋ) እስከሚቀጥለው የትምህርት አመት መጀመሪያ ድረስ (ማለትም የሠመር ወቅትን ጨምሮ) ብቁ ሆኖ ይቆያል/ብቁ ሆና ትቆያለች፣ በዚህ ጊዜ የተማሪው(ዋ) MKV ሁኔታ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለመወሰን መገምገም አለበት።

C. ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ

ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ወጣቶች ተማሪዎቻቸውን ለማስመዝገብ በሚፈልጉበት ትምህርት ቤት እና ዲስትሪክቱ ለተማሪው(ዋ) ይጠቅማል ብሎ በሚያምንበት ትምህርት ቤት ምደባን በሚመለከት ልዩነት ሲፈጠር ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ውሳኔ ለመስጠት ስብሰባ ይጠራል። ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥበት ስብሰባ ዓላማ ቤት አልባ የሆኑ ተማሪዎች ብሄራዊ የትምህርት ማእከል መስፈርት መሰረት የተማሪው(ዋ)ን ጥቅም ለማሟላት ያሉትን አማራጮች ለመገምገም ነው።

ስለ MKV ብቁነት እና ለተማሪው(ዋ) የተሻለ ጥቅም ሲባል መመዝገብ ያለበ(ባ)ትን ት/ቤት መወሰን ሁለት የተለያዩ ውሳኔዎች ናቸው። በሁሉም ሁኔታዎች፣ ተማሪው(ዋ) ወዲይውኑ መመዝገብና ት/ቤት መግባት አለ(ባ)በት፣ ስለ ብቁነት ወይም መመዝገብ ስላለ(ባ)በት ትምህርት ቤት በተመለከተ ማንኛቸውም አለመግባባት ካለ በቀጣይ መፍትሄ ያገኛል።

1. ከተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ከወጣቱ(ቷ) ፍላጎት ውጭ ካልሆነ በስተቀር በነበረ(ች)በት ትምህርት ቤት፣ ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ እንዲመዘገብ/እንድትመዘገብ ማድረግ ቤት አልባ ለሆነ(ች) ወይም ማንም ተንከባካቢ ለሌለው/ለሌላት ተማሪ የተሻለ እንደሚሆን ይታሰባል።

2. መዝጋቢው ትምህርት ቤት የወላጅ/አሳዳጊውን ወይም ተንከባካቢ የሌለውን/የሌላትን ቤት አልባ ወጣት ጥያቄ ከተቀበለ፣ ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ውሳኔ ለመስጠት ስብሰባ ማድረግ/ማካሄድ አያስፈልግም። ምዝገባን በተመለከተ የተደረገው ውይይት ቅጂ ተማሪው(ዋ)ን ይበልጥ በሚጠቅም መልኩ ወዲያውኑ ለመመዝገብ የፌደራል መስፈርቶችን በማሟላት ረገድ በቂ ነው።

3. ነገር ግን፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ደጋፊ የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች መመዝገብ በሚፈልጉበት ትምህርት ቤት እና ዲስትሪክቱ ለተማሪው(ዋ) ይበልጥ ይጠቅማል ብሎ በሚያምንበት ትምህርት ቤት መካከል ልዩነት ካለ፣ ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥበት መደበኛ ስብሰባ እንደሚከተለው ይካሄዳል፦

    a) ሰክሽን IV.A ላይ እንደተገለጸው ተማሪው(ዋ) ወዲያውኑ ይመዘገባል/ትመዘገባለች፣ እና

    b) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥበት ስብሰባ በአመቺ ጊዜ እና ምክንያታዊ በሆነ ቦታ ላይ መካሄድ አለበት።

4. በተሻለ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ የሚሰጥበት ስብሰባ መደረግ ያለበት ቦታ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች በተመዘገቡበት ትምህርት ቤት በርእሰመምህሩ/ተወካይ ጥሪ ነው።

5. ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥበት ስብሰባ የሚከተሉትን ያካትታል—

    a) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም፣ ቤት አልባ ወጣት ከሆነ(ች)፣ MCPS ቅጽ 335-77፣ የቤት አልባ ሁኔታ ማረጋገጫ ቅጽ የሞላ(ች) ተንከባካቢ፣

    b) MKV-ብቁ ተማሪ፣ አስፈላጊ ከሆነ፣

    c) ርእሰ መምህር/ተወካይ፣

    d) የተማሪ ሰራተኛ (PPW)፣

    e) አግባብነት ያለው ትምህርት ቤት እና የዋና ጽ/ቤት ሠራተኞች፥ እና

    f) MKV የግንኙነት ኃላፊ ወይም IAE ተወካይ

6. ተማሪን በተሻለ ሁኔታ እንደሚጠቅም በሚወስኑበት ጊዜ ተማሪን ያማከሉ ሁኔታዎች ማለትም በስኬታማ እንቅስቃሴ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ እና በተማሪው(ዋ) ደህንነት ላይ ከሚያሳድረው

ተጽዕኖ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁኔታዎችም ጭምር ግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል። ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል —

a) የተማሪው(ዋ) ዕድሜ፣

b) የተማሪው(ዋ) ወንድሞች እና እህቶች የሚማሩበት ትምህርት ቤት፣

c) ተማሪው(ዋ) በነበረ(ች)በት ትምህርት ቤት ያጋጠሙት/ያጋጠሚት ሁኔታዎች፣

d) የተማሪው(ዋ) የትምህርት (አካደሚያዊ) ፍላጎቶች፣

e) የተማሪው(ዋ) ስሜታዊ ፍላጎቶች፣

f) ማንኛውም ሌላ የቤተሰብ ልዩ ፍላጎቶች፣

g) የማስተማር ቀጣይነት፣

h) አሁን ባለበት/ባለችበት የኑሮ ሁኔታ የቆየ(ች)በት የጊዜ ርዝማኔ፣

i) ወደፊት የቤተሰብ ቋሚ መኖሪያ ሊሆን የሚችል ቦታ፣

j) የትምህርት ዓመቱ ሊጠናቀቅ የቀረው ጊዜ፣

k) የጉዞ ርቀት በተማሪው(ዋ) ትምህርት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ፣ እና ሌሎች ተማሪው(ዋ)ን የሚመለከቱ ትራንስፖርት ነክ ምክንያቶች፣

l) የተማሪው(ዋ) ደህንነት፣

m) በቀድሞ ትምህርት ቤት የሚሰጡ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች፤ እና

n) በቀድሞ ትምህርት ቤት የሚሰጡ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበር አገልግሎቶች።

7. የአካል ጉዳተኝነት/እክል መኖር የትምህርት ቤት ምደባን በሚመለከት ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ ላይ ሊካተት ይችላል።

a) የእያንዳንዱ ልጅ ምደባ ውሳኔ የወላጆች/የአሳዳጊዎች እና ስለልጁ-ስለልጅቱ የሚያውቁ የሌሎች ሰዎችን የግምገማ መረጃ ትርጉም እና የምደባ አማራጮችን በማገናዘብ በቡድን መደረግ አለበት።

b) ወደ ተለያዩ ቦታዎች የሚንቀሳቀሱ ቤት አልባ ልጆች ብዙ ጊዜ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በቂ ጊዜ ቆይተው የአካል ጉዳት/እክል እንዳለባቸው በትክክል ለማወቅ ስለሚያስቸግር፣ ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን ለመወሰን በሚደረግ ግምገማ ወቅት ቤት አልባ ህጻናት ላልታወቀ የአካል ጉዳት/እክል የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

8. አንድ ትምህርት ቤት ማኪኒ-ቬንቶ ብቁ የሆነ(ች) ተማሪን ምንም እንኳን በአንዳንድ ሁኔታዎች ተጨማሪ አገልግሎቶችን መስጠት ተገቢ ቢሆንም ቤት አልባ በመሆኑ(ኗ) ምክንያት ከመደበኛው ትምህርት መነጠል አይችልም።

9. ከወላጅ/አሳዳጊ ተለይቶ የሚኖር/ተለይታ የምትኖር ለ MKV-ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ለሌሎች ለ MKV-ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የሚቀርብላቸው አይነት የትምህርት ቤት አማራጮች/ምርጫዎች ሊቀርብለ(ላ)ት ይገባል።

10. ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሚሰጥበት ስብሰባ አካል እንደመሆኑ፣ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች MCPS ቅጽ 335-77፣ McKinney-Vento eligibility and Best-Interest Determinationከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር መሙላት አለባቸው። የትምህርት ቤት ምደባን በተመለከተ ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ውሳኔው MCPS ቅጽ 335-77 ላይ መገለጽ አለበት።

    a) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች በትምህርት ቤት ምደባ ውሳኔ ላይ መስማማታቸውን ወይም አለመስማማታቸውን መግለጽ አለባቸው።

    b) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች በፍላጎት ውሳኔ ስብሰባ ላይ እንዲገቡ በተወሰነላቸው የትምህርት ቤት ምደባ ካልተስማሙ፣ ርእሰ መምህሩ/ተወካይ MCPS ቅጽ 335-77A በመጠቀም ለወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ማብራሪያ መስጠት አለባቸው። ረዳት የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት ደብዳቤ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት ውሳኔውን ለማየት እና የማስተርጎም አገልግሎት የማግኘት መብትን፣ የቦርዱን እንባ ጠባቂ እና ሌሎች የጥብቅና ድጋፍ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት እንዳለው/እንዳላት በቅጹ ላይ መጠቀስ አለበት። የትምህርት ቤት ምደባ ውሳኔ መግለጫው የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል።

        1) በትምህርት ቤቱ የቀረበ ወይም ውድቅ የተደረገ እርምጃን የሚመለከት መግለጫ።

        2) ድርጊቱ ለምን እንደታቀደ ወይም እንደተከለከለ ማብራሪያ።

        3) ትምህርት ቤቱ ያሰባቸውን ሌሎች አማራጮች የሚመለከት መግለጫ።

        4) ማንኛውም ሌሎች አማራጮች ውድቅ የተደረጉባቸው ምክንያቶች።

        5) ለትምህርት ቤቱ ውሳኔ አስፈላጊ የሆኑ ከብቁነት ወይም ለተማሪው/ዋ ይበልጥ የሚጠቅመውን መሰረት በማድረግ ከሚሰጥ ውሳኔ ጋር የተያያዙ ሌሎች ማናቸውንም ሁኔታዎች የሚመለከት እውነታዎችን፣ ምስክሮች፣ እና ማስረጃዎችን ምንጮቻቸውን ጭምር መግለጽ ያስፈልጋል።

        6) ማንኛውም የግዜ ገደቦች እንዳያመልጡ ለማረጋገጥ የሚረዱ አግባብነት ያላቸው የጊዜ ሰሌዳዎች።

        7) MKV የግንኙነት ኃላፊ እና የስቴት አስተባባሪ የግንኙነት መረጃ እና ሚናቸውን የሚገልጽ አጭር መግለጫ።

D. ተመሣሣይ አገልግሎቶች

እያንዳንዱ MKV-ብቁ ተማሪ በሚማርበት/በምትማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ ለሌሎች ተማሪዎች ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተመሣሣይ የሆነ አገልግሎት ሊሰጠው/ሊሰጣት ይገባል። እንደነዚህ ያሉ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

1. ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቦርድ በተደነገገው የእግር ጉዞ ርቀት ክልል ካልሆነ(ች) በስተቀር ወደ ቀደምት ትምህርት ቤት እና ወደ አጎራባች LEAs ጭምር የትራንስፖርት አገልግሎቶችን በወቅቱ ማመቻቸት።

2. ተማሪ ተገቢውን የብቃት መስፈርት የሚያሟላ የትምህርት ፕሮግራሞች ወይም አገልግሎቶች ለምሳሌ፦ ታይትል 1 ስር የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ትምህርታዊ ፕሮግራሞች፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበር ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች፣ ቀደምት ሄድ ስታርት (Early Head Start) ጭምር፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች፣ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚመራ ሌላ ማንኛውም የቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች።

3. ከትምህርት ሠዓት በፊት እና ከትምህርት በኋላ የሚካሄዱ ፕሮግራሞች።

4. የሙያ እና የኮሌጅ ዝግጁነት ፕሮግራሞች።

5. ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጡ ፕሮግራሞች።

6. ትምህርት ቤት የምገባ ፕሮግራሞች።

E. ክሬዲት እና የእንቅስቃሴዎች ተደራሽነት

1. ርእሰ መምህራን/ተወካዮች ከስርአተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ጽህፈት ቤት እና ከትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ ጋር በመተባበር ለ MKV ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በከፊል ወይም በሙሉ ለተጠናቀቁት የኮርስ ስራዎች ተገቢውን ክሬዲት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። እንደዚህ አይነት አካሄዶች በቅድመ ትምህርት ቤት በተሟላ ሁኔታ ለተጠናቀቁ ኮርሶች ሁሉ ክሬዲት መስጠትን ያጠቃልላሉ፣ ምንም እንኳን ትምህርት ቤቱ በተለየ ዲስትሪክት ወይም ስቴት ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም፣ ከተማሪው(ዋ) የቀድሞ ትምህርት ቤት ጋር ስለ ተማሪው(ዋ) የኮርስ ስራ የተማሪው(ዋ)ን የትምህርት ሁኔታ መገምገም። በቅድመ ትምህርት ቤት በከፊል የተጠናቀቁ ኮርሶችን ማካተት፣ ከፊል ክሬዲት የተሰጠባቸው እና ሌሎች ክሬዲት የሚያስገኙ ኮርሶች መስጠታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

2. ለ MKV ብቁ ተማሪ በአካዳሚክ ፕሮግራሞች ወይም በት/ቤት በሚካሄዱ ተግባራት ሙሉ በሙሉ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ የሚከለክሉ ቅጣቶች፣ ክፍያዎች እና የማመልከቻ ወይም የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች የመመዝገቢያ ቀነ-ገደቦች ካሉ እንዲሠረዙ ይደረጋል።

F. ሪከርዶች (ማስረጃዎች)

1. ለእያንዳንዱ MKV-ብቁ ተማሪ፣ የክትባት ወይም የህክምና ማስረጃዎች፣የአካዳሚክ ሪከርዶች፣ የልደት ሰርተፍኬት፣የአሳዳጊ ማስረጃዎች እና የልዩ አገልግሎቶች ወይም ፕሮግራሞች ግምገማዎችን ጭምር ተማሪ ወደ አዲስ ትምህርት ቤት ወይም አዲስ ዲስትሪክት ሲገባ/ስትገባ

ባስፈለገ ግዜ ማግኘት እንዲቻል የተማሪ ሪከርዶችበትምህርት ቤቱ የተመዘገቡ ማናቸውም ማስረጃዎች MCPS ደንብ JOA-RA መሰረት መቀመጥ አለባቸው።

2. MKV ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ የኑሮ ሁኔታን የሚገልጹ ሪከርዶች የመረጃ ምንጭ ተደርገው አይወሰዱም፤ ስለሆነም በተማሪ ፋይል ውስጥ ካሉት ሌሎች መረጃዎች ጋር ተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል።

G. MCPS ማኪኒ-ቬንቶ ህግ የግንኙነት ተጠሪ ኃላፊነቶች

1. MCPS McKinney-Vento Act የግንኙነት ተጠሪ ለሚከተሉት ኃላፊነት አለበ(ባ)ት —

a) ቤት አልባ ልጆች እና ወጣቶች በትምህርት ቤት ሰራተኞች ተለይተው እንዲታወቁ እና ት/ቤት ገብተው MCPS ውስጥ ስኬታማ ለመሆን ሙሉ እና እኩል እድል እንዲኖራቸው ማድረግ፤

b) ነፃ ወይም የዋጋ ቅናሽ ምግቦችን እንዲያገኙ ማዘዝ፤

c) ቤት አልባ ልጆች እና ቤተሰቦች ተገቢውን የጤና አጠባበቅ፣ የጥርስ ህክምና፣ የአእምሮ ጤና አገልግሎት፣ የአደገኛ ዕፅ ሱሰኝነትን ማስወገድ እና መኖሪያን ጭምር እንዲሁም ሌሎች ተገቢ አገልግሎቶችን ጭምር እንዲያገኙ ማስተባበር፣

d) መኖርያ ቤት አልባ ወጣቶች በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያጋጥሟቸውን ማንኛውንም ስሜታዊ ቀውሶችን ለመቅረፍ ድጋፍ መስጠት፣

e) IDEA ስር እንደተገለፀው የግለሰብ የትምህርት እቅድ ለማዘጋጀት በሚካሄዱ ስብሰባዎች ወቅት ረዳት የሌለውን/የሌላትን ተማሪ መደገፍ፣

f) የትምህርት ቤት ምደባ ውሳኔዎችን ማፋጠን፣

g) ከዚህ በታች ሰክሽን G ላይ እንደተገለጸው አጋዥ የሌላቸውን ቤት አልባ ወጣቶችን መርዳት።

h) በማህበረሰቡ ውስጥ ቤት አልባ ሕፃናትን፣ ወጣቶችን እና ቤተሰቦችን ለይቶ ማወቅ፣

i) የአገልግሎቶችን መዛባት/መደራረብ ለመከላከል ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ማስተባበር፣

j) ሕጋዊ መስፈርቶች ጋር መሣለጣቸውን ለማረጋገጥ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን መከታተል፣

k) ቤት አልባ ልጆች እና ወጣቶች የሚኖራቸውን የትምህርት እና ተዛማጅ ዕድሎችን ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች ማሳወቅ፣ ይህም በልጆቻቸው ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ የማድረግ ዕድል እንደተሰጣቸው ያረጋግጣል፣

l) ትምህርት ቤቶች፣ የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች፣ የቤተሰብ መጠለያዎችን፣ የሕዝብ ቤተመፃህፍት እና ወጥ ቤቶችን ጨምሮ ቤት አልባ ልጆች እና ወጣቶች

ወላጆች/አሳዳጊዎች አዘውትረው በሚጎበኙባቸው ቦታዎች ላይ ቤት አልባ ሕፃናት ወይም ወጣቶች ያሏቸውን የትምህርትሙብቶች በይፋዊ ማስታወቂያ ማሰራጨት፣

m) የቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት ወላጅ ወይም አሳዳጊ እና ማንኛውም ጠባቂ/ኢጎዥ የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት ወደ ቀድሞ ትምህርት ቤት የሚወስድ መጓጓዣን ጨምሮ ያሉትን ሁሉንም የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲያውቅ/እንድታውቅ መደረጉን፣ አዲስ ወደ ተመረጠው ትምህርት ቤት የሚያደርስ መጓጓዣ እንዲያገኝ/እንድታገኝ እገዛ የተደረገለ(ላ)ት መሆኑን፣ እና የትምህርት ቤት ምዝገባን የሚመለከቱ አለመግባባቶች ካሉ በዚህ ደንብ መሠረት በግልግል የሚታዩ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

n) የታይትል 1 McKinney-Vento Act በተመደበው የገንዘብ መጠን አገልግሎቶች መሰጠታቸውን ለማረጋገጥ ከታይትል 1 ኃላፊዎች ጋር መስራት።

o) MKV-ብቁ ለሆኑ ህጻናት እና ወጣቶች ከስቴቱ አስተባባሪ፣ የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች፣ የትምህርት እና ተዛማጅ ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች ESOL አገልግሎቶችን፣ ሄድ ስታርት፣ ቀደም ሄድ ስታርት፣ Child Find ጭምር ማስተባበር እና መተባበር።

p) የትምህርት ቤት ሰራተኞችን፣ አገልግሎት ሰጪዎችን፣ አቀንቃኞችን፣ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ተማሪዎችን የመኖሪያ ቤት አልባ ህፃናት እና ወጣቶች የትምህርት መብቶች፣ ቤት የሌላቸው ህፃናትን እና ወጣቶችን የመለየት እና የማገልገል ፖሊሲዎች እና ሂደቶች፣ እና መኖሪያ ቤት የሌላቸው ልጆች እና ወጣቶች ልዩ ፍላጎቶች ላይ ለማሰልጠን ፕሮግራም ማዘጋጀት እና መተግበር፣ እና

q) የስቴት የመኖሪያ ቤት አልባ ልጆችና ወጣቶች ትምህርት አስተባባሪ በሚሰጠው የሙያ ማዳበር ፕሮግራም ላይ መሳተፍ።

H. የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች

1. በተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት ብዙ ቤተሰቦች በድንገት የመኖሪያ ቤታቸውን ሊያጡ ይችላሉ። በእንደዚህ ዓይነት አደጋ ወይም ሌላ አሰቃቂ ክስተት ቤት አልባ ለሆኑ ቤተሰቦች እና ተማሪዎች አገልግሎቶችን ለማመቻቸት MKV የግንኙነት ተጠሪ ከስቴት አስተባባሪዎች ጋር አብሮ መስራት ወሳኝ ይሆናል።

2. አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ፣የግንኙነት ተጠሪው(ዋ) ብዙ የተፈናቀሉ ተማሪዎች ት/ቤት እንዲመዘግቡ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጋጁ ማድረግ እና እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ሰራተኞችን በማዘጋጀት የጉዳቱ ሠለባ የሆኑትን የመለየት እና የምዝገባ ሂደት እንዲቀላጠፍ በንቃት መሥራት አለበ(ባ)ት።

3. አገናኙ (The liaison) ለ MKV ብቁ ስለሆኑ ተማሪዎች መብቶች እና አገልግሎቶችን በቀጥታ ለተጎዱት ቤተሰቦች እና ቤተሰቦችን ለሚረዱ ሰዎች ማሳወቅ አለበ(ባ)ት፥ ይህም በ MKV መብቶች ላይ የተፈናቀሉ ሰዎች በሚሰበሰቡባቸው ቦታዎች ላይ ፖስተሮችን ወይም ብሮሹሮችን መለጠፍ እና ማሰራጨትን ሊያካትት ይችላል።

I. የግምገማ እና የይግባኝ ሒደት

MCPS የመኖርያ ቤት እጦት ለሚያጋጥማቸው ህጻናት እና ወጣቶች አገልግሎቶችን በተመለከተ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት በሜሪላንድ ደንብ 13A.05.09.07 መሰረት የተፋጠነ የክርክር አፈታት ሂደት ይመሠርታል። አለመግባባቱ እና ማንኛዉም የይግባኝ ክርክር በሚፈታበት ወቅት፣ ተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት በጠየቁት ትምህርት ቤት መመዝገብ እና እዚያው እየተማረ/ች መቆየት አለበ(ባ)ት፣ እና እንደአግባቡ፣ MCPS የምግብ እና የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎት እና መጓጓዣ መስጠት አለበት።

1. የክርክር አፈታት

   a) የዚህን ደንብ አተገባበር በተመለከተ የሚነሳ አለመግባባት ወደ IAE ዳይሬክተር መቅረብ አለበት።

   b) ከወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት ከሌለው/ከሌላት ቤት አልባ ወጣት የጽሁፍ ቅሬታ ሲደርሰው/ሲደርሳት የ MKV የቤት አልባ ልጆች ግንኙነት ተጠሪ የ IAE ዳይሬክተር ከ MSDE ጋር

      1) ጥያቄውን ይገመግማል፣ እና በጋራ የሚያስማማ መፍትሄ ይፈልጋል/ትፈልጋለች፣ ወይም በ 5 የትምህርት ቀናት ውስጥ ደንቡ መተግበሩን ቀደም ብሎ ያረጋግጣል፣ እና

      2) ለወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት ለሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች ስለ IAE ውሳኔ የጽሁፍ ማብራሪያ ይሰጣል፣ወደ ይግባኝ ሰሚ ክፍል ይግባኝ የማለት መብታቸውን ጭምር፣ ይግባኝ ሰሚው አካል የት/ቤቶች ኡፐርኢንተንደንት/ተወካይ ነው።

   c) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች በውሳኔው ካልተደሰቱ፣ ወይም IAE በ 5 የትምህርት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌለው ቤት አልባ ወጣት በ 15 ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ድንገተኛ/ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ይግባኝ ለማለት ተጨማሪ ጊዜ ሊጠይቁ ይችላሉ።

2. ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) የሚቀርብ ይግባኝ

   a) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ከወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት ከሌለው/ከሌላት ቤት አልባ ወጣት የጽሁፍ ቅሬታ እንደደረሰው በ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበ(ባ)ት።

   b) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ በ 10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ(ች)፣ ወይም ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት በውሳኔው ካልተደሰተ(ች)፣ ወላጅ/አሳዳጊ/ወይም ረዳት የሌለው/የሌላት ቤት አልባ ወጣት ውሳኔውን ለትምህርት ቦርድ በትምህርት አንቀጽ §4-205(c) የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ እና በቦርድ ፖሊሲ BLBስለ ይግባኝ እና የችሎት አሰራር ህጎችላይ በተገለጸው መሰረት 30 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

c) ቦርዱ ይግባኙ በደረሰው 45 ቀናት ውስጥ ባፋጣኝ ይግባኙን ይወስናል።

3. ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ (ስቴት ቦርድ) ይግባኝ ማቅረብ

a) ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ረዳት የሌላቸው ቤት አልባ ወጣቶች በቦርዱ ውሳኔ ካልተደሰቱ COMAR 13A.01.05 ድንጋጌ መሰረት በ 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለስቴት ቦርድ በጽሑፍ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

J. ተጨማሪ መገልገያዎች/ሪሶርሶች

IAE በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ለ MKV-ብቁ ተማሪዎችን ስለመለየት እና ስለመመዝገብ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለሰራተኞች በተደጋጋሚ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶችን እና ቁልፍ ለሆኑ ቢሮዎች የመገናኛ መረጃን በማካተት መመሪያውን ይጠብቃል እና በመደበኛነት ያዘምናል። ስለ MKV ብቁነት፣ የተማሪ መብቶች፣ እና የምዝገባ ሂደቶችን የሚመለከቱ የ MCPS ህትመቶች –

1. የማኪኒ-ቬንቶ-ብቁ ተማሪዎችን የመለየት እና የመመዝገቢያ መመሪያዎች በ IAE ወቅታዊ መረጃ ይሰጣል እና

2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ መዝገብ/ሪኮርድ ማኑዋል፣በጋራ ተጠያቂነት ቢሮ/Office of Shared Accountability የሚጠበቀው እና ወቅታዊ እንዲሆን የሚደረገው ለ MKV ብቁ የሆኑ ተማሪዎችን ስለመመዝገብ መመሪያዎችን ይሰጣል።

***ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች፡-*** Swart B. McKinney-Vento Homeless Assistance Act፣ ንዑስ አንቀጽ B፣ No Child Left Behind Act of 2001(P.L. 107-110)፣ ታይትል X, ክፍል C, ንዑስ አንቀጽ B፣ ስለ ቤት አልባ ልጆች እና ወጣቶች ትምህርት፣ ታይትል I፣ ክፍል A የ 1965 የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ P.L. የተሻሻለው 114-95፣ ዲሴምበር 10 ቀን 2015 42 USC §11434A(6); የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ፣ §4-205(c); የሜሪላንድ ህግ §§13A.02.06፣ 13A.05.02.04፣13A.05.02.13፣ እና 13A.05.09

የደንቡ ታሪክ/ደንቡ የተሻሻለባቸው ወቅቶች፡- አዲስ ደንብ ኦገስት 28, 2002፣ የተሻሻለው ሴፕቴምበር 16, 2003፣ ሜይ 27, 2010 ተገምግሟል፣ ጁላይ 8, 2021 ተሻሽሏል፣ ኖቬምበር 6, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጋንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |

| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org